# ግልጽ ደብዳቤ

**የተጻፈ-------- በነሃይሉ ሻውል የወንጀል ክስ መዝገብ ተከሳሽ ቁጥር 44**
**መልእክት----በዚህ ክስ ሂደት**

አውቃችሁ-- በፍርሃት ወይም በቂም በቀል
ሳታውቁ-- በስህተት ወይም በጥቅም ስስት፣ እጃችሁን ያስገባችሁ፣ የኢሃዴግ ባለስልጣናት፣ የመንግስት ሹማምንት፣ መርማሪዎች፣ አቃቤ ህጎች፣ ዳኞችና ምስክሮች::

*ይህን መልእክት ያዘለ ደብዳቤ ስጽፍላችሁ፣ የዶለዶመው የፍትህ ሰይፍ እንዳይጨፈልቀኝ ሰግቸ፣ አልያም እራርታችሁ ልትሳሱልኝ ከጅየ እንዳልሆነ እምልላችኋለሁ:: ይልቁንም የስብእናየ መገለጫ የሆነው ቃሌ የእምነት እዳ ሆኖብኝ አገሬን--እናቴን ህዝቤን--ወገኖቸን፣ ስትጎዱብኝ ታዝቦ ማለፍ ስላልለመደብኝ ዝም ላልል ህሊናየ ስላስገደደኝ ብቻ ነው::*

*የዝች የታሪክ መታጠፊያ ቀውጢ ቀን ተግባራችሁ፣ ላንዴና ለመጨረሻ የፍትህ ስርአት እምነት ሰንኮፍ፣ ከህዝብ ስሜት ተፈንቅሎ፤ የሰላም ትግል ተስፋ ተሟጦ፣ የጨለማ ሀገራዊ ህይወት ተንዶ፣ እስካሁን ያጠፋችሁት፣ ያሰቃያችሁት ፣ያሰራችሁት፣ ያሳደዳችሁት፣ ዜጋ ሳያንስ፣ የባሰውን ተያይዘን እንዳንተናነቅ ተናንቀን እንዳንጎዳዳ፣ በቂምና በበቀል እንዳንጨቀይ ሰግቸ ነው::*

*የአንድ ህዝብ የሰላማዊ ህይወት፣ የብልጽግና፣ የሰብአዊና ፖለቲካዊ ነጻነት፣ የሚረጋገጠው የዚህ ሁሉ ዋናው መሰረት የሆነው፣ የህግ የበላይነት፣ የህግ ተአማኒነት፣ የፍትህ ስርአት ነጻነት፣ ሲኖርና ተግባራዊ ሲሆን ብቻ ነው:: ይህ ከተሸራረፈ የተረጋጋ ማህበራዊ ኑሮ መረብ ይበጣጠሳል:: መቆሚያ የማይኖረው ቀውስ አገርንና ህዝብን ያተራምሳል:: ይህ አደጋ እየታየኝ ነው እጃችሁን በዚህ የክስ ሂደት ያስገባችሁ ውስጣችሁን እንድትመረምሩ የምማጸነው::*

*ጊዜያዊ የመንፈስ ርካታን፣ ወይም ጊዜያዊ የስልጣን ጥማት ወይም ጊዜያዊ የንዋይ ድጎማን፣ ለማርካት ብላችሁ፣ በግል ስሜታችሁ ተጋግላችሁ፣ በቡድን ፍላጎታችሁ ተንሰፍስፋችሁ፣ አርቃችሁ ባለማሰብ ይህችን ሃገር--ይህን ህዝብ፣ ከማያባራ ሰቆቃ ለቅሶና ሃዘን እንዳትዳሉት፣ እራሳችሁን፣ ዘመዶቻችሁን፣ ልጆቻችሁን አንገት የሚያስደፋ የታሪክ ተጠያቂነትና ውርደት እንዳታወጡ የማሳስበው::*

*የህዝብ ዝምታን እንደ ፍርሃት፣ ማሰር መግደልና ማሳደድን፣ እንደ ጀግንነት፣ አድርባይነትን እንደ ብልጠት፣ ወስዳችሁት ከሆነ የሃቅን መንገድ ስታችኋልና ቆም ብላችሁ ራሳችሁን መርምሩ::*

*እውነት እውነት እላችኋለሁ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በመጽሀፉ መግቢያ እንዳሰፈረው « ይህ ታሽጎ ከነበረበት የፍርሃት ጠርሙስ ከፍቶ የወጣ ህዝባዊ የነጻነት መንፈስ ተመልሶ የነበረበት እሽግ ውስጥ በጉልበትና በሸብር ለመክተት በጭራሽ አይቻልም::»*

*በተከሳሾች ላይ የሃሰት ክስ መስርታችሁ፣ የሃሰት ምስክር አስመስክራችሁ፣ እንደወትሮው ሁሉ አሁንም ህግን የፖለቲካ ዱላ ልታደርጉ ዶለታችሁ:: ይህንንም በተግባር ተረጎማችሁ:: ውሳኔያችሁ ለሚያስከትለው መዘዝ ህዝብም ታሪክም ህግም ይፋረዳችኋል::*

*አንድ ተግባር ወንጀል ሊሆን የሚችለው ወንጀል ሆኖ ሲገኝ እንጅ ወንጀል እንዲሆን ስለተፈለገ አይደለም:: በሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር ሽንፈት፣ የዴሞክራሲ ስርአት አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል:: ከዚህ አልፎ የፖለቲካ ሽንፈትን እንደ ውርደት አድርጎ መቁጠርና ቂም አርግዞ በቀል መውለድ፣ ከመንፈስ ደካማነት፣ አለዚያም ከዲሞክራሲ*


breemewa@gmail.com Fax/Voice mail 206-203-0996

ግንዛቤ አልቦነት፣ ወይም በደም ውስጥ የተሰራጨ አምባ ገነንነት ውጤት ውጭ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም።

በዚህ ተንደርደሬ የተነሳሁበትን ጭብጥ በግርድፉ ልጠቃቅስ። የማነሳቸው ነጥቦች ስሜትን ለመሳብ፣ ለማግባባት የተጠፈጠፉ ሳይሆኑ ከግል ህየወቴ አንደኛ ደረጃ ምስክርነት ልሰጥበት የምችላቸው እውነታዎች ናቸው።

የከሰሳችሁዋቸው አዛውንት፣ ጎልማሶችና ወጣቶች ስልጣን የጠማቸው፣ ጥቅም ያናወዛቸው ሳይሆኑ፤ በሰላማዊ ለውጥ ብቻ የሚያምኑ፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ዘብ የቆሙ፣ የሃገራችንና የህዝባችን የተስፋ ኮከቦችና የቀውጢ ቀን ልጆች ናቸው። ህዝብን አጋፍጠው የሚሸሹ ሳይሆኑ፣ በህዝብ መሃል ቃላቸውን አክብረው ለህዝብ ልእልና የቆሙ ናቸው። ህዝብን ለመግዛት ሳይሆን፣ በህዝብ ፍላጎት ለመገዛት እራሳቸውን ያዘጋጁ ናቸው።---- ስለጥቂቶቹ የማውቀውን ልበል።

1. ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል ስልጣን የጠማው አረጋዊ ሳይሆን የህዝብን የዲሞክራሲ ጥማት ለማርካት ራሱን መስዋእት ያደረገ የሰላማዊ ትግል ጀግና ነው ። በአንድ ወቅት የያዘውን ሃላፊነት ስለማስተላለፍ ሲያወሳ አንዳችም የኔነት ጥማት፣ የስልጣን መንሰፍሰፍ፣ እንዳልነበረው ታዝቤያለሁ። ይልቁንም እንደተናገረው « ኢህአዴግ እንደተቦረቦረ ዛፍ መውደቁ ስለማይቀር ብዙም የሚያሳስብ አይሆንም ነገርግን ይህ ውድቀት በህዝብ ጫንቃ ላይ እንዳይጫንና ህዝብ እንዳይጎዳ ተጨንቀን መስራት አለብን » ብሎአል።

2. ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የሰብአዊ መብት ያለመከበር ጭንቀት፣ የሰላማዊ ለውጥ ናፍቆት እንጅ፣ እራሱን በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት አስገብቶ ለመታገል ፍላጎቱም ምኞቱም አልነበረም። የነጻነት ጎህ ሲቀድ ግን፣ ይህንኑ ለማፋጠን ሰልፉን ተቀላቀለ። ለሰላማዊው ትግል የሞራል ጉልበት ለመሆን እንጅ የስልጣን ጥማት እንዳልነበረው በተግባር አስመስክሯል። እንዲያውም « እኛ ለሰላም ቆመናል እነሱ ይተኩሱብናል በደማችን ኢትዮጵያ ትነጻለች» ብሎ የማስተማር የሞራል ስልጣን ያለው አባት ነው።

3. ዶ/ር ሃይሉ አርአያ ለእውነትና ለሃቅ ሲል ገና ከማለዳው የትግሉ አካል የሆነ እንጅ፣ የዘር ልክፍት ይዞት ህዝብን ለማፈን አልተሰለፈም። የነጻነት ጥማት የሚረካው በኢትዮጵዊነት ዙሪያ በጋራ እንጅ በደም ውፍረትና ቅጥነት አሰላለፍ እንዳልሆነ የተገነዘበ ከአድርባይነት የራቀ ንጹህ ለሃቅ የቆመ ዜጋ ነው።

4. ዶ/ር ያቆብ ወልደ ማሪያም የሃገሩ ህዝብ የፍትህ ጥማት አሳስቦት፣ የወላድ እንባ አባኖት፣ የርስ በእርስ እልቂት አደጋ ገብቶት፣ የሞቀ ኑሮውን ለህዝብ ሰላማዊ ትግልና መረጋጋት የለወጠ፣ ስልጣን ያልናፈቀው ከህዝብ ጎን ተሰልፎ ለህዝብ የቆመ ታላቅ ዜጋ ነው።

5. ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው ለስልጣን ያልተንበረከከ፣ የስልጣንን አጥር ዘሎ ለህዝብ የቆመ፣ የሃገሪቱን የቴክኖሎጅ ጥማት መርካት የሚያልም፣ ለዚህም የስርአት ለውጥ ወሳኝ መሆኑን የተቀበለ ስልጣኑን አስረክቦ ከህዝብ ጎን ለሰላማዊ ለውጥ የቆመ ዜጋ ነው።

6. ደ/ር በፈቃዱ ደገፌ የኢኮኖሚ ድክመት ለሃገር እድገትና ልማት ውጋት መሆኑን የተረዳ፣ ይህን በተግባር ለማስተካከል የተሰለፈ፣ ይህም ከሰላማዊ መንገድ ውጭ በሌላ ሊመጣ አይገባውም ብሎ ያመነ፣ አውቆ የሚያሳውቅ፣ እንጅ ለስልጣንና ለአድርባይነት እጁን ያልሰጠ ምሁር ነው።

7. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ስልጣን የጠማው፣ ገንዘብ ያሳሳው፣ ሳይሆን ሃቅ የናፈቀው፣ የዲሞክራሲ ተስፋ አብቦ አይቶ፣ ራሱን ለልማትና ለኢንቨስትመንት ለማሳተፍ


breemewa@gmail.com Fax/Voice mail 206-203-0996

የተዘጋጀ፣ ከግል ኑሮው ምቾት ይልቅ የህዝብ ነጻነት የናፈቀው የሰላማዊ ትግልና የወጣት ተሳትፎ ወሳኝነት፣ የመቻቻል ፖለቲካን አምኖ የሚያሳምን፣ የተስፋ ጎህ ቀዳጅ፣ መንፈሰ ጠንካራ ጀግና እንጅ ለስልጣን የተንበረከከ ለነውጥ የተሰለፈ አይደለም::

8. ብርቱካን ሚዴቅሳ አድርባይነትን ጨፍልቃ፣ ለህግ የበላይነት ቆማ፣ ስልጣንን በሹመት ተስፋ ሳይሆን በህዝብ ድምጽ ለማግኘት የዜግነት ግዴታዋን የተወጣች፣ ፍትህ ለተነፈጉ ዜጎች በነጻ ጥብቅና በመቆም ለንዋይና ስልጣን የማትንበረከክ መሆንዋን ያስመሰከረች በሰላማዊ ለውጥ ተስፋ የተሞላች ወጣት ነች::

9. ሙሉነህ ኢዮኤል በልበሙሉነት የመብት ረገጣን ለመቋቋም፣ እሱነቱን በፍርሃትና በአድ ርባይነት ላለመለወጥ የወሰነ፣ የስልጣን ጥማት ሳይሆን የፍትህ ርሃብ ያንገበገበው ወጣት ነው::

ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸው የቅንጅት መሪዎች ለተምሳሌነት ያቀረብኳቸው እንጅ ከደበበ እሸቱ እስከ በድሩ አደም፣ ከአባይነህ እስከ ክፍሌ ጥግነህ፣ ከታምራት እስከ አንዱአለም፣ ከንግስት እስከ የኔነህ፣ ከአለማየሁ እስከ ታዲዮስ፣ ሌሎችም ያልጠቀስኳቸው ታሪካቸው ሊዘከርላቸው የሚገባ፣ እነሱነታቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ኩራት፣ የሰላማዊ ለውጥ ተስፋዎች፣ የተስፋ ጎህ አርበኞች እንጅ ነውጠኞችና ሽብርተኞች አይደሉም::

10. ለህዝብ የሃሳብ ነጻነት ዘብ የቆሙ፣ በአድር ባይነት ሃቅን አናድበሰብስም ያሉ፣ እውነተኛነት ወንጀል ሆኖባቸው ለስር የተዳረጉ ወጣትና ጎልማሳ ጋዜጠኞች፣ የነጻነት ነበልባል በውስጣቸው የሚንቦገቦግ ሃቀኞች መሆናቸውን ከጎናቸው ሆኘ ተገንዝቤአለሁ:: የህዝብን የኢንፎርሜሽን መብት አክባሪዎች የበደልና የስቆቃ አጋላጮች እንጅ ሽብርተኞች አይደሉም::

11. ህዝብን ከተስፋ መቁረጥ እንዲወጣ ከልማትና ከድጎማ ጎን፣ ከልመናና ከርሃብ ባሻገር፣ እሱነቱን፣ የስብዕና ልእልናውን፣ እንዲያስከብር ያስተማሩ የሲቪል ማህበረሰብ አባላትን የህዝብ ተስፋ መሰረት ገንቢዎች እንደሆኑና ይህም ወንጀል ሆኖ ለካቴና መዳረጋቸውን ታዝቤያለሁ:: እኒህ የሰላማዊ ለውጥ አራማጆች እንጅ የሽብር ነዥዎች አይደሉም::

12. ለዲሞክራሲ ማበብ በተስፋ የተሰለፉ ወጣቶች፣ በፖለቲካ እምነታቸው፣ በቀንና በሌሊት ተለቅመው ተገለዋል፣ ተባረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ታስረዋል፣ ጣታቸውን ተቆርጠዋል፣ አሁንም ነጻነታቸውን ተገፈው በእስር የሚማቅቁ እጅግ ብዙ ናቸው:: እነዚህ ወጣቶች የተስፋ ጎህን መፈንጠቅ ተከትለው፣ ሰላምንና መረጋጋትን ናፍቀው፣ አድርባይነትን አሻፈረን ብለው፣ ዕንደጧፍ የሚንቦገቦጉ የሃገር ተስፋዎች እንጅ ደም የጠማቸው ሽብርተኞች አይደሉም::

በአነጣጥሮ ተኳሽ ቅልቦች ጭንቅላታቸው የተቦደሱ ሰማእታት በርካታ ናቸው:: በልጆቻቸው፣ በባሎቻቸው፣ በሚስቶቻቸው ሞትና ስደት ያረሩ ዜጎች፣ የለውጥ ፍም ሆነው በውስጣቸው ምሬትን አዳፍነዋል:: የመረረው ተስፋ የቆረጠ ለለውጥ የተዘጋጀ ህዝብ የደፋውን አንገት ቀና ሲያደርገው አይኖቹ እንደሚያቃጥሉአቸሁ ጥርጥር የለኝም::

ወገኖቸ(በተግባር ጎራ ብትለዩም ቅንጅት ፍቅር ነውና ወገኖቸ እላችኋለኑ)

የዚህ የለውጥ ባቡር ተሳፋሪ እልፍ አእላፍ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው:: በግንባር ቀደሙ ፉርጎ ከተሳፈሩት ከላይ ከጠቀስኳቸው ጋር ተሰልፈው የነበሩ ጥቂቶች ደግሞ ጓደቻቸውን ጥለው በጥቅም ወረዳ፣ በፍራቻ ጣቢያ፣ በስልጣንና በፓርላማ መናኃሪያ ተንጠባጥበው ረግፈዋል:: ስጋቸው እየሳቀ ህሊናቸው ግን ያለቅሳል::
ባቡሩ ግን እነዚህን የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኖች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጓቾች፣ የሙያ ማህበራት መሪዎችን እንደጫነ፣ በምልአተ ህዝብ ታጭቆ እየገሰገሰ፣ የተስፋ ጎህ


breemewa@gmail.com Fax/Voice mail 206-203-0996

*ቀዶለት ጉዞውን ቀጥሎአል:: ለነዚህ የሰላም ጀግኖች የኢትዮጵያ ህዝብ አንጀት ይንሰፈሰፍላቸዋል:: እናም-- ስሜቱ ሲገነፍል ማእበል ይሆናል፣ እናም-- ከሲኦል እነሱንም እራሱንም ያወጣል:: ለነሱ ገሃነም የሆነችው ኢትዮጵያ፣ ለናንተና ለተንጠበጠቡት ብቻ ገነት መሆንዋን ታቆማለች፣ የእኩልነት የፍትህና የብልጽግና ስርአት ይነግሳል::*

*ለኔና እልፍ አእላፍ ለሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ የወየኔ/ኢሃዳዴግ ተንኮልና ደባ ግልጽ ነው:: እኔ ወያኔ/ኢህአዴግን የማውቀው ከማየውና ከምሰማው ባሻገር፣ ከኢኮኖሚ ከማህበራዊና ከፖለቲካ ደባው ባሻገር፣ ለቂም በቀል መወጫ ሲል ሃሰት ማምረቱንም ጭምር ነው:: ከ14 አመት በፊት በመጀመሪያው ምርጫ ጅማሮ አካባቢ በሃሰት ወንጀሎ የማሳትመውን ጋዜጣ ምክንያት አድርጎ አሰረኝ:: ፍርድ ቤት እንዲፈታ ሲያዘው ከእስር ቤት በራፍ በመሳሪያ አስገድዶ እንደገና በሌላ እስር ቤት በማስገባት በመግደል ሙከራ ከሰሰኝ:: ይህ ሲከሽፍበትና እንዲለቅ ሲታዘዝ አሻፈረኝ ብሎ በሰው ማፈን ሌላ ክስ መሰረተብኝ:: ከሶስት አመት በፊት ሶስተኛው ታሪካዊ ምርጫ ሲቃረብ፣ በሃሰት ከሰሰኝ:: ልዩ ችሎት አቋቁሞ በአድርባይ ዳኛ ፊት ገተረኝ:: የህግ ጉዳይ ሳይሆን የቂም መወጫ ደባ መሆኑን ስለተረዳሁ አገር ጥየ ለመውጣት ተገደድኩ:: አንድ አመት ከዘጠኝ ወር ቆይቶ በሌለሁበት በቅንጅት መሪዎች መዝገብ በዘር ማጥፋት፣ በአገር ክህደትና በነውጠኝነት ከሰሰኝ::*

*የታሰሩት መሪዎች የአቃቢ ህግ ምስክር በተሰማበት በመጨረሻው ችሎት ያቀረባቸው ሁለት የሃሰት ምስክሮች እኔን 44ተኛውን ተከሳሽና 40ኛውን ተከሳሽ «በኤርትራ አስመራ ከተማ ተገኝተው የአርበኞች ግንባር ተዋጊዎችን ሰብስበው ቅንጅት ስንቅና ትጥቅ ያቀርብላችኋል፣ ውጊያውን በርትታችሁ ቀጥሉ ብለው ንግግር ሲያደርጉ ሰምተናል» ብለው በሃሰት እንዲመሰክሩ አድርጓል:: በዚህም ቅንጅትንና የቅንጅት መሪዎችን ውንጀላ ለማጠናከር ሞክሯል:: በጣም የሚገርመው ግን አሁን የምኖርበት አገር ከገባሁ ሶስት አመት ሆኖኛል ምንም አይነት የጉዞ ሰነድ አልነበረኝም ከአገር ውስጥም ወጥቸ አላውቅም::*

*ይህንን የዘረሀርኩት በኔ በቦታው ባልነበርኩት፣ በኔ ሩቅ ቦታ ባለሁት፣ በኔ ምንም ሳስፈራ በማልችል ግለሰብ ለይ እንደዚህ ወራዳ ምስክርነት ካስመሰከረ እንደ አውሬ በሚፈራቸው፣ የፖለቲካ ክስረቱን ባጋለጡ፣ ህዝብ አምኖ በመረጣቸው፣ የቅንጅት መሪዎች ጋዜጠኞችና ሌሎች አባሎች ላይ ምን አይነት የሃሰት ምስክርና መረጃ እንዳቀረበ ለዚህም የሚያበቃ የሞራል ዝቅጠት እንዳለው ለማስረዳት ብቻ ነው::*

*ወገኖቸ*

*እውነት እነዚህ ህዝብ አምኖ የመረጣቸው፣ ድጋፉን የሰጣቸው፣ የለውጥ ተስፋዎቸ ያላቸው፣ ምርጥ ምሁራንና ዜጎች ነውጠኞች ናቸው? እውነት ሽብርተኞች ናቸው? የዚህ ሂደት ተባባሪ መሆናችሁ፣ የደነዘዘ ካልሆነ በስተቀር ህሊናችሁ ሊቆስልና ሊያመረቅዝ አይገባውም? ሁለት መቶ ሰው ገድሎ ሰማኒያ ብቻ ነው ብሎ ከሚዋሽ መንግስት፣ የሃሰት ማስረጃ አቀነባብሮ ምስክሮች ደልሎና አስፈራርቶ እያስማለ የሚያስለፈልፍ መንግስትና ፓርቲ ህዝብን በፖለቲካ አመለካከቱ የሚያሳድድና የሚያስር የኢንፎርሜሽን አውታሮችን የሚያፍን መንግስትና ፓርቲ ጋር መሰለፋችሁ ውጤቱ፣ ስብእናችሁ በታሪክ ተቃጥሎና ተለብልቦ ራሳችሁንና ልጆቻችሁን ለእፍረት ማዘጋጀታችሁ እንዴት አይገባችሁም?*

*እናም---- ወገኖቸ*

*መልክቴን ተቀበሉኝ-- የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል እንደሁ እየጋለ ያቃጥላል እንጅ ይቀዘቅዛል ብላችሁ ተስፋ አታድርጉ:: ይህ የፍርድ ሂደትና ውሳኔ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ህይወት ይቀይረዋል:: ሂደቱ ቀትሎ የፖለቲካ ውሳኔ በፍርድ ስም ከተላለፈ፣ የተረገዘው የህዝብ ብሶት አመጽ ሆኖ ይወለዳል ሰላምም ትርቃለች፤ወይም የህዝብ*


breemewa@gmail.com Fax/Voice mail 206-203-0996

*ድምጽ ተሰምቶ መሪዎቻችን ከተፈቱ፣ በመቻቻል ላይ የተመሰረተ የዲሞክራሲ ሂደት ይጠናከራል። ይህችን ሃገር ከአመጽ ከሰቆቃና ስቃይ ለመታደግ ያለው አንድ አማራጭ ብቻ ነው። ይህም ህዝብን መናቅ አቁሞ የታሰሩትን ፈቶ ለሰላማዊ ድርድር መቅረብ ብቻ። ስለዚህ የዚህ መፍትሄ አካል መሆን ከታሪክ በትር መትረፍ ብቻ ሳይሆን ታሪክም መስራት ነው።*

*ስለዚህ በመቶዎች እንደሚቆጠሩት ራሳቸውን ከወያኔ/ኢህአዴግ እንዳገለሉ ጀግኖች እናንተም ታሪክ ስሩ።*

- *የወያኔ/ኢህአዴግን ውሸትና ደባ ለአለም ይፋ እንዳደረጉት እንደ ዳኛ ወልደሚከአኤል መሸሻ፣ ዳኛ ፍሬህይወት ተሾመ፣ የህግ አማካሪ ምትኩ ተሾመ፣ ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ህግ አለማሁ ዘመድኩን፣ የህግ አማካሪ አክሊሉ ሰለሞንና እንደ ሌሎችም አሻፈረን አንዋሽም የሃሰትና የደባ ወገንተኝነት ይቅርብን በሉ።*
- *ዳኞች ተከሳሾችን በነጻ በማሰናበት ከህዝብ ጋር ሆናችሁ ለፍትህ ቁሙ።*
- *አቃብያነ ህጎች ክሳችሁን በማንሳት ከታሪክ ወቀሳ እራሳችሁን አድኑ።*
- *ምስክሮች የመሰከራችሁት በሃሰትና ተገዳችሁ መሆኑን በማጋለጥ ከህሊና ወቀሳ እራሳችሁን አድኑ።*
- *የመንግስተ ባለሟሎች አድርባይነታችሁን አቁማችሁ ለህግ የበላይነት ለፍትህና ለህዝብ ፍላጎት ተገዙ።*

*እናም--- የህዝብን የለውጥ ማእበል ተቀላቀሉ፣ ወላፈኑ ሳይቀቅላችሁ ታሪክ እናንተንም ልጆቻችሁንም አንገት ሳያስደፋ፣ ከወራዶች ጎራ ራሳችሁን አግልሉ። በዚህም ወያኔ/ኢህአዴግ የናቀውን የህዝብ ቁጣና መዘዝ አብርዱ- ውጤቱ አገርን ማዳን ነውና።*

*አምላክ ሆይ ኢትዮጵያን ጠብቃት!*


breemewa@gmail.com Fax/Voice mail 206-203-0996